# ከእግዚአብሔር ፍቅር

"… እኔ የሚረባህን ነገር የማስተምርህ በምትሄድባትም መንገድ የምመራህ አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ።" (ኢሳ 48 ÷ 17)

God's Love, P.O.Box 6734 , Lee's Summit, MO, 64064. /// አዘጋጅ መላኩ ማሞ ትዕዛዙ E-mail – hello@ethiogodslove.org

**መጋቢት** 1996 March 2004 "ልጆችሽም ሁሉ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ፡ የልጆችሽም ሰላም ብዙ ይሆናል።" (ኢሳ 54÷13)


# የዘመን መጨረሻ ክስተቶች

እንግዲህ ዘመን ወደ መጨረሻው ተቃረበ። ወንጌል በምድር ገጽ በሙሉ እየተዳረሰ ነው። ድፍን ዝግ የነበሩት የእስላም ሐገሮች እንኳ ሳይቀሩ ስለ ጌታ እየሱስ ጌትነትና ስለ ዳግመኛ ምጽዓቱ ለመስማት ዕድል እያገኙ ነው። ሥጋ ለባሽ ሁሉ በፍርድ ቀን ምንም ማመካኛ እንዳይኖረው ጌታ እየሱስን ለመቀበልና ለማምለክ ዕድል እያገኘ ነው። የእግዚአብሔር ፍርድ በምድር ሁሉ ላይ ሊመጣ እንዳለውና ሁሉም ወደ እግዚአብሔር በመመለስ ራሱን እንዲያድን ያልሰማ ሰው ቁጥር እያነሰ በመሄድ ላይ ነው። ዕድሉን ያልተጠቀመ ሁሉ ወዮ የሚልበት ጊዜም ቀርቦአል።

መጽሐፍ ቅዱሳችን ስለ ደኅንነትና እግዚአብሔርን ስለማምለክ ብቻ ሳይሆን፥ ስለ ዘመን መጨረሻና ስለ ምልክቶቹም በግልጽ ያስረዳናል። ስለዚህም በ2002 (1994ዓም) በሚያዝያ ወር ደብዳቤአችን ስለ አርማጌዶን ከቃሉ ለማሳየት እንደሞከርን ይታወሳል። በዚህ ወር መልክት ደግሞ የመጨረሻውን ዘመን አስመልክቶ በትንቢተ ሕዝቅኤል ምዕራፍ 38 እና 39 የተጻፈውን ትንቢት የሚያስረዳ መልክት እናቀርባለን።

እስራኤል እአአ በ1948 ዓ/ም እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ተመልሳ ሐገር ከሆነችበት ጀምሮ፡- ግብፅ፥ዮርዳኖስ፥ኢራቅ፥ሶሪያና ሊባኖስ በሕብረት ገፍተው ወደ ባሕር ሊጥሉዋት እንደ ሞከሩ ይታወሳል። በወቅቱ የእስራኤል ሕዝብ ቁጥር 758000 ብቻ ሲሆን፥19 ሺ ብቻ ተዋጊ ወታደሮች ነበሯት። አረቦቹ ግን ለሦስት ሚሊዮን የቀረበ ኃይል ነበራቸው። ይህን የቁጥር ልዩነት ስናመዛዝን፡- 1579 የአረብ ተዋጊ ለአንድ እስራኤላዊ ተዋጊ ነበረ ማለት ነው። ነገር ግን እግዚአብሔር ድሉን ለትንሿ ለእስራኤል ሰጠ፤ እግዚአብሔር ይመስገን።

በ1967 ዓም ሶሪያ በዮርዳኖስና በሊባኖስ ተባባሪነት በእስራኤል ላይ ተነሣች፡ እስራኤልም በአጸፋ ጦርነት የግብፅን አየር ጣቢያ እስከ መደምሰስ በርትታ፡- የሱዌዝ ባሕረ ሰላጤን ፥ ሲናንና ጋዛን እንዲሁም ጥንታዊዋን እየሩሳሌምን (Old Jerusalem) ያዘች። በዚያን ጊዜ ግብፅ ለመደራደር ወደ ተባበሩት መንግሥታት አቤቱታ አቀረበች። እስራኤል ግን ጎላን ሐይትን ጨምራ ከሶርያ ማረከች። ይህም ክንዷን ጨምሮ አበረታ። በዚህም መልክ ቀደም ሲል በተገኙት ድሎችና በ1973 ዓም የዮም ኪፑር ዕለት ጦርነት በተፈጸሙት ትንቢቶች ፥ እስራኤል እየተጠናቀቀች መጣች፤ ጌታ እግዚአብሔር ይመስገን። ከዚህ በኋላ፡- በትንቢተ ዘካሪያስ 14÷11 "ሰዎችም ይኖሩባታል፥ ከዚያም ወዲያ እርግማን አይሆንም፡ እየሩሳሌምም ተዘልላ ትኖራለች"ተብሎ እንደ ተጻፈው፡ተዘልላ ለመኖር እየፈጠነች ናት። ይህ የሚያሳየን ጌታ ለባሪያው ለያዕቆብ የገባውን የተስፋ ቃል በየወቅቱ እየፈጸመ መሆኑን ነው። የእግዚአብሔርን መንግሥት የምትጠባበቅ የጌታ ቤተ ክርስቲያን ይህንን ማስተዋልና በጥሞና መከታተል አለባት

ይህ ዘመን እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የገለጸልንን የዘመን መጨረሻ ትርዒትና ተዋንያን ለይተን ልንረዳ የሚገባበት ወቅት ነው።

በመጽሐፍ ቅዱሳችን፡- በዖሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 10፥ የሰውን ዘር አመጣጥ በዝርዝር እናያለን። በትንቢተ ሕዝቅኤል 38 እና 39 ደግሞ የዘመን መጨረሻ የጦርነት ትርዒት እንዴትና በእነማን እንደሚደረግ እንማራለን።

በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት፡- በመጨረሻው የዓለም ጦርነት ዋናዎቹ ተሳታፊዎች ዘጠኝ ናቸው። እነርሱም፡- ጎግና ማጎግ፥ሞሳሕና ቶባል፥ፋርስ፥ኢትዮጵያ ፉጥ (ሊቢያ) ጋሜር፥ ቱርጋማ ናቸው። የእነዚህን ጐሣዎች አመጣጥ ለመረዳት፥ ያፌትንና ልጆቹን መረዳት አስፈላጊ ይሆናል።



ማጎግ የያፌት ልጅ ነው። ሞሳሕና ቶባልም የያፌት ልጆች ሲሆኑ የሚገኙትም ከመካከለኛው ምሥራቅ በስተ ምሥራቅ ነው። እነዚህ በዮሐንስ ራእይ 20÷8 ሰይጣን "በአራቱም በምድር ማዕዘን ያሉትን ሕዝብ፥ጎግንና ማጎግን፥እንዲያስታቸው ለሰልፍም እንዲያስከትታቸው ይወጣል ፤ ቊጥራቸውም እንደ ባሕር አሸዋ የሚያህል ነው" የተባለላቸው ናቸው። ሩሲያ ደግሞ ከጥቁር ባሕር በስተ ሰሜንና ከካውከስ ተራራዎች በስተ ምሥራቅ፥በደንበሪ በኩል፥ ጥቁር ባሕር ጥጉን ያለውን ሕዝብ ማለታችን ነው። እነዚህ በመጽሐፉችን ኤስኩቴስ በመባል የሚታወቁ፥ በጭካኔአቸው ወደር የሌላቸው፥ ዛሬ ደቡባዊው የሩሲያ አካባቢ ከሚሆነው ሥፍራ ያሉት ሕዝብ ናቸው

ሔሮዲዎስ የተባለው ታሪካዊ ጦረኛ፥ ትሽሪ በተባለው መጽሐፉ፥ ኤስኩቴሶችን ሲቲያኖች(Scythians) ይላቸዋል። እርሱም ሐገራቸውን ወርሮ ካሸነፈ በኋላ እንዲህ ሲል ጽፎአል። (የሲትያኖች ክረምት ብርዱ ወደር የለውም። ከብርዱም የተነሣ ፥ ውኃ ብትደፉ ወዲያው በረዶ ይሆናል ይልና፡-ሕዝቡም እንደ ክረምቱ ልበ በረድ ነው፤እጅግ ጨካኞች ናቸው፤ በጦር ሜዳ የገደሉትን የመጀመሪያውን ሰው ደም ይጠጡታል። የሚቹንም ሰው የራስ ቅል ለንጉሣቸው ይወስዳሉ)ብሏል፤ እነዚህን ሕዝቦች ከዘመናችን የዓለም ካርታ ጋር ስናስተያይ፡- ፓክስታን፥ ካዛክስታን፥ኪርግዝስታን፥ታጂክስታን፥ ቱርክሜኒስታንና ኡዝቤክስታን ሆነው እናገኛቸዋለን። ሁሉም ከሩሲያ በስተ ደቡብና በዩክሬን የሚገኙ ናቸው።

የያፌት ስድስተኛው ልጅ ፥ የማጎግ ወንድም የሆነውን ሞሳሕን ደግሞ በዘፍጥረት 10÷2 እና በ1ኛ ዜና መዋዕል 1÷5 እናገኛለን። የሞሳሕ ሕዝብ፡-ከወንድሞቹ ከያዋንና ከቶቤል ሕዝብ ጋር ሆነው፥ልዩ ልዩ የነሐስ ዕቃዎችንና ብረት፡ነክ የጦር መሣሪያዎችን ለዓለም ያስተዋወቁ ናቸው። በሰውም ይነግዱ ነበሩ የሞሳሕ ተወላጆች በተለያዩ ስሞች ይታወቃሉ። ሙስኪ፥ሙስኮ፥ሙስኮዊ፥ ዛሬ ደግሞ ሞስኮ የተባለው ነው።ሔሮዲዎስ ስለ እነዚህ የጻፈው በአምስተኛው ክፍለ ዘመን ነበር ።

በዘፍጥረት 10÷2 የተጠቀሰው ቶቤል በዚህ ዘመን አይቤሪያውያን የሚባሉት፡ የቶቤላውያን አባት ነው። እነዚህም ከጥቁር ባሕር በስተ ምሥራቅ የሚገኙ ሕዝቦች ናቸው።

ፋርስ (ፔርሲያ) ደግሞ የሴም ዝሪያ ነው። ኢሳይያስ በምዕራፍ 21÷2፤ ዳንኤልም በትንቢቱ ስለ ባቢሎን በሰፊው ጽፈዋል። ባቢሎን በዚያን ጊዜ ሰው ሊደርስበት እንዴት ቻለ የሚያሰኝ ሥልጣኔ ነበራቸው። ፔርሲያ በ1936 ዓም የስም ለውጥ በማድረግ ኢራን ተባለ።

ኢትዮጵያ በመጽሐፍ ቅዱሳችን መሠረት፡- የካም የበኩር ልጅ፥የፉጥን ወንድም፥ የኩሽ ልጆችን የሚወክል ስም ነው፡ (ዘፍጥረት 10÷6) ጆሴፈስ ፊላጵዮስ እንደሚያሳየን፡- አራቱን የካም ልጆች፡- ኩሽ፥ ምጽራይ፥ ፉጥንና ከነዓንን በመጥቀስ፥ ኩሽ ኢትዮጵያ መሆኑን ይነግረናል። እነዚህ ከ450 ዓዓ በፊት ጀምሮ ከግብፅ በስተ ደቡብ መኖራቸው የታወቀ ጥቁር ሕዝብ ናቸው። ይህ ከታሪክ ጋር የማይጋጭ ድምዳሜ ነው ማለት ይቻላል። **aithiopai** የሚለው የግሪክ ቃል፡- "የተቃጠለ ፊት" ማለትም "ጥቁር ፊት" ማለት ሲሆን፡- ሱዳን የተባለውም እንዲሁ ነው። ሱዌዳን የሚለው የአረብ ቃል፡ (አስወድ የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር) ሲሆን፥ ትርጉሙ ጥቁሮች ማለት ነው። ይህም ኩሽ ከግብፅ በስተ ደቡብ የሚገኝ ጥቁር ሕዝብ ነው ከሚለው ጋር በትክክል ይስማማል። (በቅርቡ በዜና የሰማነው የሱዳን፥ የኢትዮጵያና የመን ሕብረት፡- እንዲሁም የአረብ ሊግ ኢትዮጵያን ለአባልነት ማጨት ወሬ የምን ቅድመ ዝግጅት ይሆን?)

ሊቢያ በዘፍጥረት 10÷6 የተመለከተው ፉጥ ነው። ሐገሪቱን በ440 ዓዓ፥በአሁኑ ሰም የሰየመው ላባን የተባለው የፉጥ አጎት ነበር።

በተጨማሪ፡-ትንቢተ ሕዝቅኤል 38÷6"በሰሜን በኩል ጎሜርና የቤትቶጋርማ ምድር ጦረኞች ከእርሱ ጋር ናቸው" ሲል ስለ ጎሜር ይናገራል። እርሱም የያፌት የበኩር ልጅ፥ የማጎግ፥ የሞሳሕና የቱባል ወንድም ነው። ጎሜር በዓለም ታሪክ ውስጥ ሲሜሪያን (Cimmerian) ተብለው ይጠቀሳሉ። እነዚህም ከአሲሪያ ጋር ብዙ የተዋጉ ፥ ጦረኛ ሕዝብ ናቸው።

በዘፍጥረት 10÷3 የተጠቀሰው ቶጋርማ በፈረስ ንግድ ይታወቅ የነበረ ሕዝብ ነው። እነዚህ ሁሉም በሕዝቅኤል 38 እና 39 የተዘረዘሩ የመጨረሻው ጦርነት ዘማቾች ናቸው። እንግዲህ ወገኖቼ፡- እነዚህንና የአረብ መንግሥታት ሕብረት

(Arab League of Nations) በሚል ስም የተባበሩትን ወደ ፊትም የሚተባበሯቸውን የዓለም መንግሥታት ሂደት፡- ከትንቢት ቃል አንጻር በአግባቡ እንድንረዳ ጌታ ይጠብቅብናል:: በመጨረሻው ዘመን በሚፈጸመው ትንቢት ዋና ተዋናይ የሚሆኑትን ሕዝቦች ጂኦግራፊያዊ ቦታቸውንና ባሕላቸውን መረዳት፡- ምን እንደሚገፋፋቸው ለመረዳት ይጠቅማልያም በማስተዋል ለመፀለይ ይረዳል:: “በምድር ያሰራችሁት በሰማይ የታሰረ ይሆናል" በሚለው መሠረት፡- በፀሎታችን የሴይጣንን ሥራ በስሙ ጠርተን ለመፀለይ ያስችለናል::

“እንግዲህ እንደ ጥበበኞች እንጂ ጥበብ እንደሌላቸው ሳይሆን እንዴት እንድት መላለሉ በጥንቃቄ ተጠበቁ ፡ ቀኖቹ ክፉዎች ናቸውና ዘመኑን ዋጁ::” ተብሎ ተጽፎአልና:: (ኤፌሶን 5፥15-16)

(Signs of The Times በሚል ርዕስ፥ በፓስተር ራፍ ቢከም ተጽፎ Body of Christ News በሚባል የዴንቨር ክርስቲያኖች ጋዜጣ ከወጣ መልዕክት ተወስዶ የተዘጋጀ)

**www.ethiogodslove.org**



# የቃል ኪዳኑ ታቦት

የብሉይ ኪዳን መቅደስ ማዕከል ቅድስተ ቅዱሳን ይባላል:: ይኸውም ከሁሉ ይልቅ የተቀደሰና የከበረው፥ክፍል ሲሆን፥ታቦቱ የሚኖረው በዚሁ ክፍል ነው:: ታቦትም፡ የተሰበረው አሥርቱ ትዕዛዛት የተጻፉበትን ጽላት የያዘ፥እግዚአብሔር በሕዝቡ መሐከል የተገኘበት ፥ በወርቅ የተለበጠ ማጥን (cabinet) ነው::

ታቦቱ ወደሚኖርበት ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ክፍል መግባት የሚችል የተወሰነው ሊቀ ካሕኑ ብቻ ነው:: ይህም የምርጫ ጉዳይ ሳይሆን በታቦቱ ላይ የነበረው የእግዚአብሔር ቅዱስ ኃይል በዘፈቀደ ሊቀረብ ስለ ማይቻል ነው:: ሊቀ ካሕኑም እንኳ ተገቢውን መመሪያ ተከትሎ ከነፃና ከተዘጋጀ በኋላ በብዙ ጥንቃቄ መግባት ነበረበት:: ያውም በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ነበር::

# አዲስ ኪዳን

ብሉይ ኪዳን ሕጎችን፥ ትዕዛዛቱንና ሥርዓቱን በማሟላት ላይ የተመሠረተ የመቅደስና የታቦት ሥርዓት ሲሆን፡- መሪውም እንደ እኛው ጉድለት ያለበት ሊቀ ካሕን ለመሆን የተመረጠ ሰው ነው ስለ ሆነም ሕዝቡን ከእግዚአብሔር ጋር ለዘለቄታው ሊያስታርቅ አልተቻለውም ጌታ አዲሱን ኪዳን የገለጠው በዚህ ምክንያት ነው::

በአዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር ከሰው ጋር መገኘት ሚስጢር የተለየ ነው:: መጽሐፍ እንዲህ ይላል፡-

“እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ፤ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፤ ስሙም 'ዐማኑኤል' ተብሎ ይጠራል::” <u>ዐማኑኤል</u> ማለትም “<u>እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው</u>” ማለት ነው:: (የማቴዎስ ወንጌል 1፥23 አ/ት)



“ክርስቶስ የእውነተኛዪቱ ድንኳን ምሳሌ ወደ ሆነችውና በሰው እጅ ወደተሠራችው መቅደስ አልገባም ነገር ግን አሁን ስለ እኛ በእግዚአብሔር ፊት ለመታየት፥ ወደ እርሷ ወደ ሰማይ ገባ::”
(ዕብ 9፥24)

እንግዲህ በአዲስ ኪዳን ፡- እግዚአብሔር የሚገኘው ፥ የድንግሊቱ ልጅ አማኑኤል በሚገኝበት ቦታ ነው ማለት ነው::በብሉይ ኪዳን ያለ ሊቀ ካሕኑ ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ መቅረብ እንደማይቻል ሁሉ፡- በአዲሱ ኪዳን ደግሞ አ<u>ማኑኤል</u> ከሆነው ከጌታ እየሱስ በቀር ወደ እግዚአብሔር አብ መቅረብ አይቻልም:: ከመላዕክትና ከጻድቃን አንድም በዚህ ሊረዳ የሚችል የለም:: ምክንያቱም ጌታ ራሱ እንዲህ ሲል አስጠንቅቆናል:: “እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፡ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም::”
(የማቴዎስ ወንጌል 14፥6)

በብሉይ ኪዳን ሊቀ ካሕን አንድ ብቻ ነበረ:: ብዙ ሌዋውያን ካሕናት ሲኖሩ፡- ሊቀ ካሕኑ ግን ከአንድ በላይ እንዲሆን አልተፈቀደም:: በአዲስ ኪዳንም እንዲሁ ነው:: በእግዚአብሔርና በሰው መሐከል ብቻውን አማላጅና ሊቀ ካሕን የሆነው፡ በእግዚአብሔር አብ ቀኝ በክብር የተቀመጠውና <u>ሥልጣን ሁሉ</u> የተሰጠው ጌታ እየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው:: ከእርሱ በቀር ስለ ሰዎች ኃጢአት የሞተና ከሙታን የተነሣ፥<u>ሥልጣንም ሁሉ</u> የተሰጠው ማንም ስለ ሌለ ከቅዱሳንም ሆነ ከመላዕክት ለዚህ የሚበቃ የለም::

“እንግዲህ በሰማያት ያለፈ ትልቅ ሊቀ ካሕናት የእግዚአብሔር ልጅ እየሱስ ስላለን፥ጸንተን ኃይማኖታችንን እንጠብቅ:: ከኃጢአት በቀር በነገር ሁሉ እንደ እኛ የተፈተነ ነው እንጂ በድካማችን ሊራራልን የማይችል ሊቀ ካሕናት የለንም:: <u>*እንግዲህ ምሕረትን እንድንቀበል በሚያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን ጸጋ እንድናገኝ ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት እንቅረብ*</u>::” (ወደ ዕብራውያን 4 ፥ 14-16)

የብሉይ ኪዳን መቅደስ ሕንፃው ሲሆን፡- የአዲስ ኪዳን መቅደስ ግን ጌታ እየሱስን በጌትነቱና በአዳኝነቱ የተቀበለ ሰው ልብ ነው::

በብሉይ ኪዳን መቅደስ ከታቦቱ እኩል የሚከበር ምንም ነገር የለም:: በአዲስ ኪዳን መቅደስ (በሰው ልብ) ከጌታ ከእየሱስ እኩል መከበር የሚገባው፡- ምንም፥ ማንም ሊኖር አይገባውም:: ካለ ግን ኃጢአት ነው:: ያም ከሴይጣን ነው::

በእየሱስ ክርስቶስ የሆነው አዲስ ኪዳን ከታቦቱ ሥርዓት ስለ መሻሉ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡-

“<u>ሕጉ ምንም ፍጹም አላደረገምና</u>፥ ስለ ዚህም የምትደክም <u>የማትጠቅምም ስለ ሆነች</u> የቀደመች ትዕዛዝ <u>ተሽራለች</u> ወደ <u>እግዚአብሔርም የምንቀርብበት የሚሻል ተስፋ</u> ገብቶአል (ተገልጾአል)”
(ወደ ዕብራውያን 7፥18-19)

**“መዳንም በሌላ በማንም የለም እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች (ከየሱስ) ሌላ የለምና::” (የሐዋሪያት ሥራ 4፥ 12)**

“ክርስቶስ አሁን ላሉት መልካም ነገሮች ሊቀ ካሕናት ሆኖ በመጣ ጊዜ በሰው እጅ ወዳልተሠራችው፥ ከዚህ ፍጥረት ወዳልሆነችው ታላቅና ፍጹም ድንኳን ገባ:: የገባውም የፍየሎችንና የጥጃዎችን ደም ይዞ አይደለም፤ ነገር ግን የዘላለም ቤዛነት ሊያስገኝ የራሱን ደም ይዞ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ገባ::” (ዕብራውያን 9፥ 11-12) “ክርስቶስ የእውነተኛዪቱ ድንኳን ምሳሌ ወደ ሆነችውና በሰው እጅ ወደ ተሠራችው መቅደስ አልገባም፤ነገር ግን አሁን ስለ እኛ በእግዚአብሔር ፊት ለመታየት፥ወደ እርሷ ወደ ሰማይ ገባ::”
(ዕብ 9፥24)

“ሰው አንድ ጊዜ ሊሞት ከዚያም በኋላ በፍርድ ፊት ሊቆም ተወስኖበታል:: ክርስቶስ የብዙ ሰዎችን ኃጥአት ለመሸከም፥እንዲሁ አንድ ጊዜ መሥዋዕት ሆኖ አል፤ ሁለተኛ ጊዜም ይገለጣል፤ ይህም ለሚጠባበቁት እንጂ ኃጢአትን ለመሸከም አይደለም::” (ዕብ 9፥27-28)

... ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ጠላቶቹ የእግሩ መረገጫ እስኪሆኑ ድረስ ይጠብቃል፤ ምክንያቱም <u>በአንዱ መሥዋዕት</u> <u>እነዚያን የሚቀደሱትን ለዘላለም ፍጹማን አድርጎአቸዋል</u>::” (ዕብራውያን 10፥ 14)

ወገኔ ሆይ፡- አዲስ ኪዳንን አዲስ ካደረጉት ምክንያቶች አንዱ የእንስሳትን ደም መሰዋት መቅረቱና የመቅደስ ሥርዓት መለወጡ ነው:: ምክንያቱም፡- ጌታ እየሱስ ክርስቶስ “የፍየሎችንና የጥጃዎችን ደም...(ሳይሆን)፤...የዘላለም ቤዛነት ሊያስገኝ የራሱን ደም ይዞ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን <u>ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ</u>...” ስለ ገባና የዓለምን ኃጢአት ላማስወገድ በቂ የደም ካሣ ስለ ከፈለ ነው:: ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን::

መጽሐፍ ስለጌታችን እየሱስ “በውነት ደዌያችንን ተቀበለ ሕመማችንንም ተሸክሞአል፤እኛ ግን እንደ ተመታ በእግዚአብሔርም እንደ ተቀሠፈ እንደ ተቸገረም ቈጠርነው:: ...በማስጨነቅና በፍርድ ተወሰደ፤ ስለ ሕዝቤ ኃጢአት ተመትቶ ከሕያዋን ምድር እንደ ተወገደ ከትውልዱ ማን አስተዋለ? ... እግዚአብሔርም በደዌ ያደቀቀው ዘንድ ፈቀደ ፤ <u>*ነፍሱን ስለ ኃጢአት መሥዋዕት ካደረገ በኋላ ዘሩን ያያል*</u>፥...”ይላል:: (ትንቢተ ኢሳይያስ 53፥4-10)

ዘሩም የሰው ልጅ በሙሉ ነው እንጂ አይሁድ ብቻ አይደሉም:: የሰው ልጅ በሙሉ የኃጢአቱ ዕዳ ተከፍሎለታል:: ይህ ዕውነት ነው:: ይህ ዕወነት ግን ለሁሉ አይሠራም:: ይህንን ዕውነት በዕምነት ለሚቀበሉት ይሠራል:: የማያምኑት ግን በኃጢአታቸው ይሞታሉ:: መጽሐፍ እንዲህ ይላል፡-

“የእርሱ ወደ ሆነው መጣ፥የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉትም:: ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው ፤ እነርሱም ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም” ይላል:: (የዮሐንስ ወንጌል 1፥11-13) <u>የመጣልህን አዳኝ እየሱስን ተቀብለኸዋል</u>? እንዲሁም፡-

“እውነት እውነት እልሃለሁ፥ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ *በቀር* የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም” (የዮሐንስ ወንጌል 3፥3) <u>ዳግመኛ ተወልደሃል</u>?

## <u>ፀሎት</u>፡-

ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፥ ዳግመኛ መወለድ እሻለሁ:: የእየሱስ ሞት ኃጢአቴን እንዲያነፃልኝ አምኜ እቀበላለሁ:: ደኅንነትን ስጠኝ:: ስለ ስምህ:: አሜን::

እየሱስ ጌታ ነው:: ጌታ ይባርክህ::